# የዶ/ር አቢይ ፈተናዎችና እድሎች

(*ወንድወሰን ተክሉ-የኢትዮሚዲያ አምደኛ*)

*ሰላም ውድ እድምተኞቼ እንደምን ሰነበታችሁሳ? ለውድ የክርስትና እምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን ለበዓለ ሆሳእና ክብረ በዓል በሰላም አደረሳችሁ ስል ለትንሳኤ ብርሃን በዓሉም በሳላም ያድርሳችሁ እያልኩ ወደ መጣጥፌ አመራለሁ፡፡*

***መነሻ ነጥብ-የዶ/ር አቢይ ጠ/ምኒስትርነት*

*ከህዳር 2017 ጀምሮ መጀመሪያ በኦሮሚያዋ የጊንጪ ከተማ ተማሪዎች የጪሊሞን ደን «ለባለሀብት» ተሸጦ መጨፍጨፍን በመቃወም የተጀመረው አመጽ ቀጥሎም የአዲስ አበባን ማስተር ፕላን በመቃወም ተተክቶ መላ ኦሮሚያን እና ብሎም የአማራን ክፍለሀገራትን ያጠልቀለቀው ህዝባዊ አመጽ ከሁለት ዓመት ትግል በሃላ ገዢውን የኢህአዴግ ፓርቲ ከህወሃት ፈረስነት ነጻ ማውጣት የቻለበት ደረጃ ላይ መድረሱን እንረዳለን፡፡*

*ሕዝባዊው ትግልና አመጽ በ26የኢህአዴግ አገዛዝ ያልታየንና ሊታይም ይችላል ተብሎ በፖለቲከኛውና በተንታኞችም ያልተገመተን የህወሃት ተፈጣሪ የሆነውን ኦህዴድና ብአዴንን በጌታችን ሲሉትና ፈረስ ሆነው ሲጋለቡለት ለነበረው ህወሃት ላይ አምጸው እንዲነሱ ማድረግ ከማስቻሉም በላይ በቲም ለማ የሚመራውን የኦህዴዱን ዶ/ር አቢይ አህመድን ለጠ/ምኒስትርነት በማብቃት ደረጃ ላይ መድረሱን እያየን ነው፡፡*

*የ42 ዓመቱ የኦህዴዱ ሊ/ር ዶ/ር አቢይ አህመድ በህወሃት ተጠፍጥፎ የተፈጠረውን ኢህአዴግ ከፈጣሪው እጅ ነጥቆ ለመሸፈር የሚያበቃውን የድርጅቱን ሊ/ርነት ስልጣን የተቆናጠጡት በህዝባዊው ትግል ውጤት እንጂ በራሳቸው በዶ/ር አቢይም ሆነ በድርጅታቸው ኦህዴድ የተናጥል ትግልና ጥንካሬ እንዳልሆነ ሂደቱ በግልጽ ይመሰክራል፡፡*

*ዛሬ በእለት ሰኞ አዲሱ የኢህአዴግ ሊ/ር ዶ/ር አቢይ አህመድ የሀገር ውስጥ ተቃዋሚዎችና የውጭ ሀገር አምባሳደሮችና ዲፕሎማቶች በእንግድነት በሚገኙበት በፓርላማው የሀገሪቱ ጠ/ሚ የሚያደርጋቸውን ቃለ መሀላ ፈጽመው ስራቸውን በይፋ እንደሚጀምሩ ይጠበቃል፡፡*

*እኚህ አንደበተ ርቱእ እና በእድሜያቸውም ገና በአፍላ ጉልምስና ላይ ያሉት ዶ/ር አቢይ አቢይ ለሀገር መሪነት መሪነት ደረጃ የበቁት በህዝባዊው ትግል ውጤት በመሆኑ የተነሳ የተጣለባቸው ተስፋ እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑም ጎን ለጎን በሃላፊነታቸው የሚጠብቃቸውም ፈተና እጅግ ወሳኝ እና ሃይለኛ መሆኑን እሳቸው ወደ ስልጣን ከመጡበት አስቸጋሪውና ፈታኙ የወቅቱ የኢትዮጵያ ሁኔታ አንጻር መናገር ይቻላል፡፡*

*ኢትዮጵያ ያለችበትን ፈታኝ ሁኔታን በሚገባ የተረዱትና ብሎም ሲገልጹ የነበሩት ዶ/ር አቢይ በጠ/ይ ምኒስትርነታቸው ቀላል የሚባል ስራ ሳይሆን እጅግ ከበድ ያለ እና በይዘቱም ውስብስብነት የሚታወቀውን የሀገሪቱን ዘርፈ ብዙ ችግርና ቀውስ በአግባቡ መክተው መፍትሄ በመስጠት ሀገራዊውን ቀውስና ችግር መፍታት ይቻለኛል ብለው ባያምኑ ኑሮ እራሳቸውን ለእጩነት እንደማያቀርቡ በመገመት ዶ/ር አቢይ ብዙ ለውጥ ያመጣሉ ብለን ልንገምት እንችል ይሆናል፡፡*

*የእሳቸው ወደ ጠ/ይ ምኒስትርነት ስልጣን መምጣት የገዢውን ፓርቲ እና ደጋፊዎቹን ጎራ ለሁለት እንደከፈለ ሁሉ ከተቃዋሚውም ጎራ ቁጥርና ይዘታቸው ይነስና ይለያይ እንጂ የተቃወሙ መፍጠር መቻሉንም የምንክደው አይደለም፡፡*

*ግዮን ውብሸት የተባለ ጸሃፊ የዶ/ር አቢይን መመረጥ የደገፍኩበት ምክንያት ብሎ ካሰፈረው ባለ ስምንት ምክንያቶች ውስጥ «ዶ/ር አብይ የአንድነትን ጥቅም ማወቅ ብቻ ሳይሆን ከአንድነት*

ውጪ ሌላ አማራጭ እንደሌለ ደጋግሞ ሲናገር አዳምጫለሁ። ("እንደህዝብ ከመደመር ውጪ ሌላ አማራጭ የለንም።") ከመናገርም ባለፈ ባለፉት 27 ዓመታት በጎሪጥ እንዲተያዩ ተፈርዶባቸው የነበሩትን የአማርኛና የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያንን ለማቀራረብ እሱና አቶ ለማ የወሰዱት እርምጃ ምን ያህል ከመናገር ባለፈ ከልብ የመነጨ የአንድነትና የእርቅ ፍላጎት እንዳላቸው ያሳያል» ካለ በሃላ ቀጠል አድርጎ ደግሞ « ከኦሮሚያ ክልል የመታወቂያ ካርዶች ላይ ብሄር የሚለውን ማስወጣታቸው፣ ከብአዴን ጋር የጀመሩት አስደናቂ መናበብ፣ በኢትዮጵያ ታሪክ የመደብ እንጂ የብሄር ጭቆና እንዳልነበረ እንደሚያምኑ የሚፈነጥቅ መግለጫ ማውጣታቸውና ለሎች መሰረታዊ እርምጃዎችን ለአብነት ያህል መጥቀስ ይቻላይ። የዶክተሩን ንግግር ለመጥቀስ ያህል "ታሪክ ለነገ ድልድይ ከሆነ መልካም ነው። ታሪክ ዛሬን የሚያበላሽብን ከሆነ ግን ችግር አለ» በማለት የዶ/ሩን ወደ ስልጣን መምጣት የደገፈበትን ምክንያት ገልጿል፡፡

ያቀረባቸው ነጥቦች ውሃ የሚቃጥሩ በመሆናቸው ቀንጭቤ ላቀርበው ብችልም የዶ/ሩን ወደ ስልጣን መምጣት ሀገራችን ካለችበት ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ውጥንቅጡ የወጣ ችግር አንጻር መፍትሄ ናቸው ብለው ተስፋ ያደረጋቸው ሰዎች ቁጥር አብዛኛው ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የውጭ ሀገራት ጭምር መሆናቸውን መረዳት የቻልነውና እምንከደው እውነታ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡

በኢትዮጵያዊያን እና ብሎም በውጭ ሀገራትም ጭምር ታላቅ ተስፋ የተጣለባቸው ዶ/ር አቢይ አህመድ በእርግጥ የተጣለባቸውን ሃላፊነት በአግባቡ መወጣት ይችላሉ የሚለው ጥያቄ ወሳኝ የሆነ ሲሆን ለዚህም ለዶ/ር ቀጣይ ስራ ህዝብ የሚጠብቅባቸውን ታላቅ ስራ እንዳይወጡ እንቅፋት የሚሆናቸውን እና ብሎም ሊፈጽማቸው የሚችሉትንም በጎ ስራዎችን በሁለት ከፍዬ ላስቀምጠው እወዳለሁ፡፡

**1ኛ-ከዶ/ር አቢይ ጠ/ይ ምኒስትርነት የምንጠብቀው ምንድነው?

ሀገራችንና ብሎም ሰፊው ህዝብ ከዶ/ር አቢይ እጅግ በርካታ ነገሮችን በተስፋ እንደሚጠብቅ ቢታወቅም እሳቸው ግን ሊፈጽሙ ይችሉ ይሆናል ብዬ ይበልጥ የማተኩረው ወደ ስልጣን የመጡበትን ምክንያትና መንገድ መሰረት በማድረግ እንደሆነ እረዳለሁ፡፡

ህወሃት ሀገራችንን ላለፉት 26ዓመታት ሲገዛ የፈጸማቸው ሰናይም ይሁኑ እኩይ ተግባራቱ፣ህዝቡን ለመግዛት የዘረጋቸው መንግስታዊ መዋቅሮቹ፣ህገ መንግስቱና ልዩ ልዩ ፖሊሲዎቹን የተገበረው አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በሃላ ያፈለቃቸው አዲስ አስተሳሰቦች ውጤት ሳይሆን ገና ከደደቢት ዋሻው እያለ ወጥኖ የተነሳለትን ዓላማ እንደተገበረ እንረዳለን፡፡

የዶ/ር አቢይ አህመድ ራይና ዓላማ ምንድነው የሚለውን ጥያቄ ስንሰነዝር በፍጥነት የምናገኘው መልስ የሁለት ኋይሎችን ዓላማና ራእይ ምንድነው ብለን እንድንጠይቅ የሚያደርገን መልስ ነው፡ ፡ አዎን ያም ሁለት ኋይል የቲም ለማ ቡድን እና የህዝባዊው አመጽ የተባሉት ሁለት ሃይሎች ሲሆን የእነዚህ ሁለት ኋይሎች ራእይና ዓላማ ምንድነው ብለን እንድንጠይቅ እንገዳደለን ማለት ነው፡፡

ዶ/ር አቢይ አህመድ እንደ የቲም ለማ ቡድን ውጤት መሆናቸውና የህዝባዊው ትግል ውልድ ሆነው ለስልጣን የበቁ እንደመሆናቸው መጠን በተቆናጠጡት የመሪነት ስልጣን ላይ ሆነው የሚፈጽሟቸው ተግባራቶች የእነዚህን ሁለት ሃይሎች ራእይና ዓላማን በሕገ መንግስቱ አንቀጹ 74 ቁጥር ከ1-13 በተዘረዘሩት የስልጣን ደረጃ ለመፈጸም ይጥራሉ ወይም ይፈጽማሉ ብለን እንድንጠብቅ ሂደቱ ያስገድዳል፡፡

ሆኖም ይህን ስል -ማለትም ዶ/ር አቢይ ለስልጣን ያበቃቸውን የቲም ለማን ቡድን እና የህዝባዊውን ትግል ራእይና ዓላማን ይፈጽማሉ ብዬ ስገልጽ ዶ/ሩ ከህዝባዊው ትግል ሲቀርብ የነበሩትን ሀገራዊና ህዝባዊ ጥያቄዎች በሙሉ እንዲሁ በቀላሉ ይመልስሉ ማለቴ ሳይሆን ስልጣን

ከያዙ በሃላ የሚፈጽሟቸው ተግባራቶች ለስልጣን ያበቃቸውን ኋይል ዓላማና ራእይ ለመፈጸም ይነሳሉ ማለቴ እንጂ ያለምንም ሳንካ፣ተቃውሞና እንቅፋት ይፈጽሙታል ማለቴም አይደለም፡፡

«የሀገራችን ክብርና ህልውና ከማንኛችንም ስልጣንና ክብር በላይ ነው» የሚሉት አቶ ለማ መገርሳ «እኛ ሀገርን እንደሀገር የማስቀጠልና ህልውናዋን የመጠበቅ ሃላፊነትና ግዴታ ያለብን ነን» በማለት የፌዴራሉን ስልጣን ለመያዝ የወሰኑበትን ምክንያት ሀገር ለማዳን ሲሉ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ተሰናባቹ ጠ/ም አቶ ኋይለማሪያም ደሳለኝ ወደ ስልጣን የመጡበት ምክንያትና መንገድ በራሱ ሰውዬው በስልጣን ቆይታቸው የሰሩትን እና የፈጸሙትን ሃላፊነት የጎደለው ተግባር እንዲፈጽሙ እንዳደረጋቸው መዘንጋት የለብንም፡፡ አንዳችም የመሪነት ራእይና ህልም ከዓላማ ጋር ያልነበራቸው አቶ ኋይለ ማሪያም ለታማኝነት ስራ ለጠ/ሚኒስትርነት ሲመደቡ በቆይታቸው ታማኝ ሆነው ያገለገሉት የመደባቸውን ወገን /ህወሃትን/ እንጂ በስልጣናቸውና በችሎታቸው ህጉ በሚፈቅድላቸው መጠን የኢትዮጵያን ህዝብ እንዳላገለገሉ አይተናል፡፡

የዶ/ር አቢይ ስልጣን በህወሃት በጎፈቃድና ምድባ የተሰጠ ሳይሆን በኢትዮጵያ ህዝብ እልህ አስጨራሽ ትግልና ከፍተኛ መስዋእትነት በተፈጠረው የቲም ለማ ቡድን ከፍተኛ ትግልና ትንቅንቅ ያለህወሃት ፍቃድ የተገኘ በመሆኑ ዶ/ር አቢይ ታማኝነታቸውን እና አገልጋይነታቸውን የሚያደርጉት ለህሊናቸው፣ለህዝብና ለድርጅታቸው ኦህዴድ በማድረግ ሀገራዊ ሃላፊነታቸውን እንደሚወጡ መገመት ይቻላል፡፡

የህዝባዊው ትግል ውጤት የሆነው የቲም ለማ ቡድን ካነገባቸው ራእይና ዓላማዎች ውስጥ ወሳኝ ነጥቦች ውስጥ
*የህወሃትን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ የበላይነት መለወጥ
*የፖለቲካ ምህዳሩን አስፍቶ ሁሉን አሳታፊ ስርዓት ማድረግ
*የመናገርና የመጻፍ መብት ተከብሮ ነጻ የመገናኛ ብዙሃን መፈጠር
*በህዝብ መካከል የተፈጠረውን ልዩነትና መራራቅን አስተካክሎ ሀገራዊ አንድነትን መገንባትና ማጠናከር
*የፖለቲካ እስረኞችን በሙሉ የመፍታት
*መከላከያውና ደህንነቱን የብሔር ተዋጽኦን የሸፈነ ማድረግ
*የፍትህ ስርዓቱን በማስተካከል የህግ የበላይነትን እና ፍትሃዊነትን ማስፈን
* ህገ መንግስታዊ መብትና ጥቅሞች ለዜጎች ሁሉ በእኩል ተፈጻሚ እና ተከባሪ ማድረግ የሚሉት ነጥቦች ከሚጠቀሱት ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ኦህዴድ ባበለፈው ድርጅታዊ ጉባኤው ባስተላለፈው ባለ11ነጥብ ድርጅታዊ የአቋምና የስራ መግለጫ ውስጥ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ነጥቦች የታቀፉ ከመሆናቸውም በላይ ነጥቦቹ የህዝባዊው ትግል መሰረታዊ ጥያቄዎችም እንደሆኑ ይታወቃል፡፡

የኦህዴድ ሊ/ር የነበሩት አቶ ለማ መገርሳ ከአቶ ኋይለማሪያም ደሳለኝ ስልጣን መልቀቅ በሉት መባረር ማግስት ባደረጉት ምስጢራዊ ውሳኔ ከያዙት የኦህዴድ ሊ/ርነት ስልጣን እራሳቸውን ዝቅ አድርገው በምክትልነት ቦታ በማስቀመጥ የዛሬውን ጠ/ም ዶ/ር አቢይን ሊ/ር መንበር ያደረጉበት ዋና ምክንያት ያነገቡትን የለውጥ ዓላማ ለመተግበር የሀገር መሪነቱን ስፍራ የግድ መያዝ ስላለባቸው ሲሆን እራሳቸውን ለመሪነት ያላጩበት ምክንያትም የተወካዮች ምክር ቤት አባል ባለመሆናቸው እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ሆኖም የቲም ለማ ቡድን አካል የሆኑት ዶ/ር አቢይ ወደ ስልጣን መምጣት ቡድኑ የተነሳለትን ዓላማ ለመፈጸም እንጂ አንዳችም ድጋፉን ላልሰጠችው ህወሃት እንደ አቶ ኋይለማሪያም ደሳለኝ ታዛዥና ታማኝ ሆኖ ህወሃትን ብቻ ለማገልገል እንዳልሆነ መታወቅ አለበት፡፡

2ኛ- የዶ/ር አቢይ ፈተናዎች -

ህዝባዊው ትግል ዛሬ ዶ/ር አቢይን ለጠ/ይ ምኒስትርነት ካበቃ በሃላ በወሳኝ ምእራፍ ላይ እንዳለ እናያለን፡፡ ቀሪውንም የትግል ሂደት ዶ/ሩን ያማከለ የትግል ስልትና እስትራቴጂ አውጥቶ በመጋዝ የቀረውን ድል ለመጎናጸፍ ትግሉን ማጧጧፍ አለበት የሚል እድምታ ያለ ሲሆን ይህም የህዝባዊውን ትግል ጥያቄ ይመልሳሉ የተባሉትን ዶ/ር አቢይን ከኋላ ጀርባ ሆኖ መስጠት ያለበትን ሃይልና ድጋፍ እጅግ አስፈላጊነትን መግለጽ ያስፈለገው ከሚገጥማቸው ፈተና አንጻር ነው፡፡

በእግጥ ዶ/ር አቢይ ከሁለት አቅጣጫ የተከፈተ ፈተና እንደሚጠብቃቸው ጠንቅቀው ይረዳሉ ብዬ አምናለሁ፡፡ ሁለቱ ተጻራሪ ፈታኝ ሃይሎችም ተስፋ ያደረጋቸው ሰፊው ህዝብ እና በአንጻሩም ተስፋዬን አጨለሙብኝ ያላቸው የህወሃት ሃይልና ብሎም የኢህአዴግ ድፍጅታዊ ማእከላዊነትና አይዲኦሎጂ ሲሆን ሁለቱም ኋይሎች ወሳኝ የሆነ ኋይል ያላቸው ከመሆኑ የተነሳ ፍጥጫውን በውጥረት የተሞላ እንደሚያደርገው ይገመታል፡፡

ህወሃት እራሱ ባጸደቀው ሕገ መንግስት አንጻር ዶ/ር አቢይ ሀገሪቷን ለመምራት በሚንቀሳቀሱበት ሂደት የመጀመሪያው ሰለባ የሚሆነው ኢ-ህገ መንግስታዊ ስልጣንና ሀብት ያካበተው ህወሃት ከመሆኑ ዶ/ሩ ከባድ እንቅፋትና ተቃውሞ እንደሚጠብቃቸው ይገመታል፡፡

የቲም ለማ ቡድን ሕገ መንግስታዊ መብት፣ስልጣንና ጥቅም በህገ ደንቡ መሰረት ይፈጸም የሚለው ጥያቄ ተተገበረ ማለት ከሁለት ዓስርተ ዓመታት በላይ የዘለቀው የህወሃት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ የባልይነትና ሞኖፖሊ ተንኮታኮተ ማለት ሲሆን ይህን መከላከያውን፣ደህንነቱን እና ኢኮኖሚውን የተቆጣጠረው ህወሃት እነዚህን ጡንቻዎቹን እስኪነጠቅ በዝምታ ይቀበላል ብሎ ማሰቡ የዋህነት ነው፡፡

በዛሬይቷ ኢትዮጵያ ውስጥ ከጥቃቅና እስከ ትልቁ ባለው ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ህግን ተክትሎ የሚደረግ ውሳኔ ሁሉ በህገ ወጥ መንገድ የተገነባውን የህወሃትን ጥቅም የሚገረሥ ስ ከመሆኑ አንጻር ዶ/ሩ ለስልጣን ባበቃቸው ህዝባዊ ትግል መደገፍ ለጥያቄ የሚቀርብ አይሆንም፡፡

የሲቪል አስተዳደሩን የተነጠቀው ህወሃት በቀጣይ በወታደሩ፣በደህንነቱና በኢኮኖሚው ተጠቅሞ የለውጡን ሂደት ለማጨናገፍ እንደሚጥር ከታሰበ የዶ/ር አቢይ አመራርና ህዝባዊውም ትግል በቅድሚያ ማነጣጠር ያለበት በእነዚሁ የህወሃት የጀርባ አጥንት በሆኑት ተቋማቶች ላይ ሊሆን ይገባል፡፡

የኢህአዴግን ድርጅታዊ የጋራ ስራን ህገ ደንብ እንቅፋትነት በፓርላማ እና በድርጅቱ ውስጥ ባሉት አብላጫ የኦህዴድና የብአዴን አባላት መሰረት ህወሃት የዶ/ሩን ውሳኔና ተግባራቶችን ለማገድ እንደሚቸግራት ይገመታል፡፡ የህወሃት ብቸኛው ዶ/ሩን የምታደናቅፍበት ኋይልና ጉልበት ከኢህአዴግ አይዲኦሎጆካዊ ማሰሪያና ድርጅታዊ ህገ ደንቡ ይልቅ የወታደሩ፣ደህንነቱና የኢኮኖሚው ክፍል ሲሆን የብአዴንን ሙሉ ድጋፍና የደቡቡን ግማሽ ድምጽ ድጋፍ ያገኙት ዶ/ር አቢይ አመራር በድምጽ ብልጫ ያሻውን ውሳኔ የማሳለፍ ችግር አይገጥመውም ተብሎ ይገመታል ፡፡

እንደ ህገ መንግስቱ የጠ/ም ስልጣን መሰረት ዶ/ር አቢይ በርካታ የሆኑ ወሳኝ ውሳኔዎችን ያለ ፓርላማው እና ፓርቲው ፍቃድ ማሳለፍ እንደሚችሉ የሚያሳይ ሲሆን በተለይም ደግሞ በፓርላማው የኦህዴድና ብአዴን አብላጫ መቀመጫ መያዝ ለዶ/ር አቢይ ታላቅ እገዛና ድጋፍ እንደሚሰጣቸው ይታመናል፡፡

ህዝባዊው ትግል የኦህዴድን እና የብአዴን ሃይል ማርኮ ከጎኑ ማሰለፍ ችሏል፡፡

የዶ/ር አቢይም ለስልጣን መብቃት የህዝባዊው ትግል የመጨረሻ ግብና ድል ሳይሆን የትግሉ ማዳረሻ ግማሽ ግን ወሳኝ የሆነ ድል እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ይህንን ግማሽ የሆነን ግን ወሳኝ ድልን በማቀፍ፣በመያዝና ከጎኑ በማሰለፍና በድሉ ሳይዘናጋ  ትግሉን አቀጣጥሎ ከገፋ ዶ/ር አቢይን ከህወሃት ለውጡን አጨንጋፊ እጅና ጥቃት መከላከል ከማስቻሉም በላይ ለተነሳለት ሁለንተናዊ ስርነቀል ለውጥ ለድል እንደሚበቃ በማወቅ ሲያካሂድ የቆየውን ትግል በስልትና በትጋት መቀጠል እንዳለበት በመደምደሚያ መልክ ላስገነዝብ እወዳለሁ፡፡
ቸር እንሰንብት!
---------------
ጥያቄያችሁን ወይም አስተያየታችሁን በteklu7@gmail.com ጻፉልኝ በአክብሮት እመልሳለሁ

ኢትዮሚድያ - Ethiomedia.com
April 1, 2018